| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | "ጦማረ ፡ ክዋኔ ፥ መግቢያ ፦ ኢ.ሀ.ሥ.አ.ን ፡ እናስተዋውቃችኹ ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ነሐሴ ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ቍ.2016-005 |
| ማስታወሻ ፤ | "ክዋኔ" ፡ ዐምድ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ክዋኔ

CONSTITUTION | دستور

*[በዚህ ፡ ዐምድ ፥ ስለ ፡ ክዋኔ ፡ (ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት) ፡ ጕዳይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ ይቀርቡበታል ። ]*

## ጦማረ ፡ ክዋኔ ፥ መግቢያ ፦

# ኢ.ሀ.ሥ.አ.ን ፡ እናስተዋውቃችኹ!

---

ነሐሴ ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ።

ይህ ፡ የመዠመሪያ ፡ ጦማረ ፡ ክዋኔ ፥ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነትን ፥ ወይም ፡ ባጪሩ ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ.ን ፡ ያስተዋውቃል ።

( ላዲስ ፡ አንባቢ ፡ ያስቸግሩ ፡ ይኾናል ፡ ያልናቸው ፡ ቃላት ፡ እጦማሩ ፡ መዝጊያ ፡ ላይ ፡ ተፈቶዋል ። )

ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ በ1966-1967 ፡ ዓ.ም. ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አቀጣጥሎት ፡ የነበረውን ፡ ለውጥ ፡ ወታደራዊ ፡ ደርግ ፡ በጨነገፈበት ፡ ወቅት ፥ የሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባላት ፡ እውጭ ፡ ሀገር ፡ ይገኙ ፡ ለነበሩት ፡ ለሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ደጋግመው ፡ በላኩላቸው ፡ የዐደራ ፡ መልእክት ፡ መሠረት ፥ በሐምሌ ፡ ወር ፡ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ ለንደን ፡ ላይ ፡ የተቋቋመ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነታዊ ፡ አካል ፡ ነው ።

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ዐላማ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፦

1ኛ ፤ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ ወይም ፡ ገዢነቱን ፡ እንዲያስከብር ፤

2ኛ ፤ ዐዲስ ፡ ክዋኔ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንዲሠራ ፥ ወይም ፡ ሀገሩን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በዐዲስ ፡ ክዋኔ ፡ እንዲከውን ፤

3ኛ ፤ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥቱን ፡ እንዲመሠርት ፡ ወይም ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ኩነቱን ፡ እንዲከውን ፡

ትግሉን ፡ አስተባብሮ ፡ ለድል ፡ ማብቃት ፡ ነው ።

ስለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ አመሠራረት ፡ እና ፡ ስለ ፡ መሠረታውያን ፡ ደንቦቹ ፡ በቂ ፡ መረጃን ፡ ከመርበቢያው ፡ ከ ፦

www.slttunhzb.net

ማግኘት ፡ ይቻላል ።

ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ የመብት ፡ አባል ፡ ነው ፤ በመብቱ ፡ መሥራትን ፡ ወይም ፡ አለመሥራትን ፡ የራሱ ፡ ምርጫ ፡ ይወስነዋል ።

እላይ ፡ ለሦስት ፡ ከፍለን ፡ የገለጽነውን ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ዐላማ ፥ በሚከተሉት ፡ ጦማሮች ፡ በዝርዝር ፡ እንተነትነዋለን ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።

አስቀድማችኹ ፡ ለማጥናት ፡ የምትሹ ፡ ኹሉ ፥ ከኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መርበቢያ ፡ ከ ፦

www.slttunhzb.net

ሙሉ ፡ መረጃን ፡ የሚሰጡ ፡ ሰነዶች ፡ አሉላችኹ ፤ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፡ ሥራው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ብዙውን ፡ ጒዳይ ፡ በዝርዝር ፡ ዐትቶላችኺል ።

ካቅማችን ፡ እና ፡ ከኀላፊነታችን ፡ በላይ ፡ ያልኾነውን ፡ ማንኛውንም ፡ ጥያቄ ፡ ወይም ፡ አስተያየት ፡ ብታቀርቡልን ፥ እንደ ፡ አባልነታችን ፡ ባክብሮት ፡ እንመልሳለን ፤ በቀጥታ ፡ ከኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መልስ ፡ ለምትሹ ፡ ደግሞ ፡ በእ-ጦማር ፡ አድራሻችን ፡ በ ፦

sh1@ttomar.net

ልትጽፉልት ፡ ትችላላችኹ ።

ጦማሮቻችን ፡ ኹሉ ፡ የሚጻፉት ፡ በትኽክለኛው ፡ የፊደል ፡ አጠነቃቀቅ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በተቻለ ፡ መጠን ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶችን ፡ ለማስወገድ ፡ ሞክረናል ፥ ለዚህም ፡ "ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የተባለው ፡ የጽሑም ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ (software) ፡ ረድቶናል ፤ እናንተም ፡ እንድትሠሩበት ፡ እናበራታችኺለን ፤ መገኛው ፦

www.awde-qelem.net ነው ፥

PC ፡ ካላችኹ ፥ በ Windows ፡ ምግባር ፡ (operating system) ፡ ላይ ፡ ይሠራል ።

---

<u>የቃላት ፡ መፍቻ ፤</u>

**ሀገራዊ** ፡ ( *ስም* ) ፤ የሀገር ፡ ሠሪ ፥ የሀገር ፡ ባለቤት ፥ ዐምሐራ ፡ (citizen, *n.*)

**ሀገራዊ** ፡ (ቅጽል) ፤ የሀገር ፡ (citizen, *adj.*)

**መርበቢያ** ፤ የመረብ ፡ ገጽ ፡ መገኛ ፡ (web ፡ site)

**ሥልጡን** ፤ ሥልጣን ፡ ያለው ፥ የብጤውን ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ የራሱን ፡ መብት ፡ የሚያስከብር ፥ ሥሉጥ ፡ (civil)

**ሥልጡንሕዝባዊ** ፤ የሥልጡንሕዝብ ፡ (democratic)

**ሥልጡንሕዝብ** ፤ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፥ የብጤውን ፡ መብት ፡ አክብሮ ፡ የራሱን ፡ መብት ፡ የሚያስከብር ፥ ሥሉጥ ፡ ሕዝብ ፡ (democrat)

**ሥልጡንሕዝብና** ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፥ አንዱ ፡ የሌላ ፡ ብጤውን ፡ መብት ፡ በማክበር ፡ ወንፈል ፥ ጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ ዐብሮ ፡ የሚኖርበት ፡ ሥልጡን ፡ ሥርዐት ፡ (democracy)

**ጦማር** ፤ መልክት ፡ (mail ፡ ወይም ፡ post)

**እግዚእና** ፤ ገገርነት ፡ (sovereignty)

**ኢትዮጵያዊ-ሀገራዊ** ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊነት ፡ ያለው ፡ (Ethiopian citizen)

**ዐምሐራ** ፤ ዐም ፡ = ፡ ሕዝብ ፥ ሐራ ፡ = ፡ ነጻ ፥ በተገናኝ ፡ ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ የሀገር ፡ ባለቤት ፥ እግዚእና ፡ ያለው ፥ የሀገር ፡ ሠሪ ፥ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ (citizenry)

**ዐምሐራዊ** ፡ ( *ስም* ) ፤ የዐምሐራ ፡ አባል ፥ ሀገራዊ ፡ (citizen, *n.*)

**ዐምሐራዊ** ፡ ( *ቅጽል* ) ፤ የዐምሐራ ፥ ሀገራዊ ፡ (citizen, *adj.*)

**ስያስ** ፤ ዘዴ ፡ (policy)


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።

**ስያሳ** ፤ "ፖለቲካ" ፡ (politics)

**ስያሳዊ** ፤ "ፖለቲካዊ" ፡ (political)


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።